# ALL NATIONS GOSPEL PUBLISHERS



Copyright ANGP

www.angp-hb.co.za

info@angp.co.za

# የሰው ልብ

ወይም

## የመንፈሳዊ ልብ መስተዋት

### (በአሥር ሥዕሎች አማካኝነት የቀረበ ተምሳሌታዊ መልእክት)

ይህ እ.ኤ.አ. በ1732 ለመጀመሪያ ጊዜ በፈረንሳይ አገር የተዘጋጀው መጽሐፍ፥ በ1929 በሬቨሬንድ ጄ. አር. ግሽዌንድ አማካኝነት ለአፍሪካ ለወንጌል ስርጭት በሚስማማ መልኩ ተሻሽሎና ተዘጋጅቶ ቀርቧል። ከዚያም «ወንጌል ለሁሉም ሕዝብ አሳታሚዎች» («All Nations Gospel Publishers») በተባለው ድርጅት አማካኝነት ከ250 በሚበልጡ ዓበይት ቋንቋዎች ሊተረጐም በቅቷል። በዛሬውም ጊዜ አሳታሚው ድርጅት ይህንን መጽሐፍ ወንጌል በማስረዳት ለሚያገለግሉባቸው 127 አገሮች በማሰራጨት ላይ ይገኛል። በመሆኑም የየትኛውም ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦችም ሆኑ፥ ወይንም የማንኛውም መደብና ሃይማኖት ተከታዮች፥ በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ እየተመሩባት ይገኛሉ። ከዚህም የተነሣ፥ ያነበቧት ሁሉ ከክርስቶስ ከመወለዱ ከ586 ዓመታት አስቀድሞ በነቢዩ ሕዝቅኤል፥ «አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ ... ሕዝብም ትሆኑኛላችሁ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ» (ሕዝ. 36፡26-28) ተብሎ እንደ ተነገረ፥ የጠለቀ መንፈሳዊ እውቀት ከመገብየታቸውም በተጨማሪ የእግዚአብሔር ቃል ለሰው ልጅ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ለመረዳት በቅተዋል።

COPYRIGHT

ISBN 0 - 908367 - 23 - 6

E-MAIL: info@angp.co.za
ALL NATIONS GOSPEL PUBLISHERS
P.O. Box 2191, PRETORIA, 0001, R.S.A.
(A Gospel Literature Mission financed by donations)
(Reg. No. 1961/001798/08)

Copyright ANGP

# የሰው ልብ

## የእግዚአብሔር መቅደስ ወይስ የሰይጣን ቢሮ?
## (1ኛ ዮሐ. 3፡4-10)

ይህን መጽሐፍ ስታነብ ሳለህ፥ እባክህን ይዘቱ ራስህን እንደምትመለከትበት መስተዋት ዓይነት ስለመሆኑ ልብ በል። አረማዊ ወይም ክርስቲያን፥ በክርስቶስ የማታምን ወይም ኮብላይ ብትሆን፥ በዚህ መጽሐፍ ረዳትነት ራስህን እግዚአብሔር እንደሚያይህ አድርገህ ታያለህ። «ሰው ፊትን ያያል፥ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል» (1ኛ ሳሙ. 16፡7)። እግዚአብሔር የሚያየው ትክክለኛውን እኛነታችንን ነው።

ሰይጣን የውሸት አባት ነው። ወንዶችንና ሴቶችን ወደተሳሳተ አቅጣጫ ለመምራት የብርሃንን መልአክ መስሎ የሚቀርብ የጽልመት አለቃና የዚህ ዓለም አምላክ ነው። እንደ ቀድሞው ሁሉ በዚህም ዘመን፥ የክርስቶስን ሐዋርያት በመምሰል ተሸፋፍነው የሚመጡ፥ በርካታ ሐሰተኛ ሐዋርያት ይገኛሉ። ሰይጣንም ራሱ የብርሃንን መልአክ በመምሰል መልኩን ስለሚለውጥ፥ ይህ የሚያስደንቅ አይሆንም (2ኛ ቆሮ. 11፡13፥ 14)። የዚህ ዓለም አምላክ የሆነው ሰይጣን፥ ሰዎችን በጨለማ ውስጥ ስለሚያኖራቸው፥ እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው ወይም ክርስቶስ እነርሱን ለማዳን እንደሞተ አይተው ለማስተዋል አይችሉም (2ኛ ቆሮ. 4፡4)። ኃጢአተኞችና የማያምኑ ሰዎች መንፈሳዊ ሙታን ስለሆኑ፥ የእግዚአብሔርን ነገር በተመለከተ ዓይነ-ስውራን ናቸው። በዚህም ዓለም ክፉት ተገዝተዋል (ኤፌ. 2፡1-2)። ዓይኖቻቸው በሆነ መንገድ ተከፍተው የጥፋት ጐዳናቸውን ካልተመለከቱ በስተቀር፥ ወደ ዘላለማዊ ውድመት እየገሠገሡ ናቸው። «ኃጢአት ሠርቼ አላውቅም» የሚል ሰው ራሱን ያታልላል። «ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» (1ኛ ዮሐ. 3፡8)። «እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን

Copyright ANGP

ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል» (ያዕ. 4፡7-8)።

ይህንን መጽሐፍ ስታነብና በውስጡ የሚገኙትን ሥዕሎች ስትመለከት፥ የራስህን ልብ ለማየት ትችላለህ። የእግዚአብሔር የምርምር ብርሃን የልብህን ሁኔታ እንዲያሳይህ ፍቀድለት። ኃጢአት እንዳለብህ አምነህ ተቀበል እንጂ ኃጢአት አልሠራሁም አትበል፤ የእግዚአብሔር ቃል ይህንኑ ይመሰክራልና፡- «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፥ ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» (1ኛ ዮሐ. 1፡1-10)። «የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።»

በሰይጣን ወይም በእግዚአብሔር ተገዝተሃል፤ የኃጢአት ባሪያ ወይም የእግዚአብሔር አገልጋይ ነህ። ኃጢአት ሕይወትህን ከተቆጣጠረው ለርዳታ ወደ እግዚአብሔር ጩኽ እንጂ «ኃጢአት የለብኝም» አትበል። እርሱም ኃጢአተኞችን ለማዳን፥ ባንተም ላይ የነገሠውን የሰይጣንና የኃጢአት ኃይል ለመስበር ወደዚህ ዓለም በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ነፃ ያወጣሃል። እርሱ አዳኛችን ነው። ምሥጢራትን ሁሉ፥ የተሰወሩትን አሳቦችና የሕይወትህን ተግባራት በሚያውቅ አምላክ ፊት ነህና፥ ራስህንም ሆነ ተግባራትህን ከእግዚአብሔር ልትሸሽግ አትችልም፤ «ጆሮን የተከለው አይሰማምን? ዓይንን የሠራው አያይምን?» [መዝ. (94)፡9]።

«እግዚአብሔር ልቡ በእርሱ ዘንድ ፍጹም የሆነውን ያጸና ዘንድ ዓይኖቹ በምድር ሁሉ ይመለከታሉና» (2ኛ ዜና 16፡9)።

«ዓይኖቹ በሰው መንገድ ላይ ናቸው፥ እርምጃውንም ሁሉ ያያል። ኃጢአትን የሚሠሩ ይሰወሩበት ዘንድ ጨለማ ወይም የሞት ጥላ የለም» (ኢዮብ 34፡21፥ 22)።

Copyright ANGP

«ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር ፤ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና» (ዮሐ. 2፡24)።

ስለሆነም፥ «መተላለፉ የቀረችለት ኃጢአቱም የተከደነለት ምስጉን ነው። እግዚአብሔር በደልን የማይቆጥርበት፥ በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው ምስጉን ነው» [መዝ. (32)፡ 1-2]።

# የሥዕሎቹ መግለጫ

## የመጀመሪያው ሥዕል

ይህ ሥዕል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኃጢአተኛ ተብሎ የተገለጸውን ዓለማዊና ኃጢአተኛውን ወንድ ወይም ሴት ያመለክታል። ይህን ዓይነቱም ሰው በዚህች ዓለም ክፋት፥ በተፈጥሮአዊ ፍላጐቶችና በከንቱ ምኞቶች ቁጥጥር ሥር የዋለ ነው። በመሆኑም ሥዕሉ፥ ኃጢአተኛ ልብን እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያይ ቁልጭ አድርጎ የሚያቀርብ እውነተኛ ሥዕል ነው። ለምሳሌ የቀሉና የፈዘዙ ዓይኖች፡- በምሳሌ 23፡29-33 የተጠቀሰውን የሰካራምነት ሕይወት ያመለክታሉ፤ «ዋይታ ለማን ነው? ኃዘን ለማን ነው? ጠብ ለማን ነው? ጩኸት ለማን ነው? ያለምክንያት መቁሰል ለማን ነው? የዓይን ቅላት ለማን ነው? የወይን ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለምን? ... ወደ ወይን ጠጅ አትመልከት በቀላ ጊዜ፥ መልኩም በብርሌ ባንጸባረቀ ጊዜ፥ እየጣፈጠም በገባ ጊዜ። በኋል እንደ እባብ ይነድፋል፥ እንደ እፉኝትም መርዙን ያፈሳል። ዓይኖችህ ጋለሞታዎችን ያያሉ፥ ልብህም ጠማማ ነገርን ይናገራል።»


በዚህ ሥዕል ከምናየው ሰው ራስ ሥር የሚገኘው ልብ፥ የኃጢአቶች ማዕከልና የመራቢያ ክፍል እንደመሆኑ፥ በሰው ልብ የሚገኙትን የተለያዩ ኃጢአቶች የሚወክሉ እንስሳት ሲተራመሱበት እንመለከታለን። እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ በኩል «የሰው

Copyright AHGP

ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል?» ይላል (ኤር. 17፡9)።

ኢየሱስም ራሱ «ከውስጥ ከሰው ልብ የሚመጣ ክፉ አሳብ፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጐምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸውና፤ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውንም ያረክሰዋል» በማለት ያጠናክረዋል (ማር. 7፡21-23)።

Copyright ANGP



1. የኃጢአተኛ ሰው ልብ

1. ብርቅዬው ወፍ (ፒኮክ) - የዚህ ወፍ ውበት በሁሉም ዘንድ የተደነቀ ቢሆንም፥ በዚህ የሰው ልብ ውስጥ ግን የትዕቢትን ኃጢአት ያሳያል። በአንድ ወቅት የእግዚአብሔር ልዩ የብርሃን መልአክ የነበረው ሉሲፈር በትዕቢት ምክንያት ሥልጣኑን አጥቶ የእግዚአብሔር ጠላት ዲያብሎስ ሆኖአል (ኢሳ. 14፡9-17፤ ሕዝ. 28፡12-17)።

   ትዕቢት ከልብ እምብርት ይመነጭና ራሱን በብዙ መንገዶች ይገልጻል። አንዳንድ ሰዎች በብልጽግናቸው፥ በትምህርት ደረጃቸው፥ ሰውነታቸውን ኃፍረት በሌለበት ሁኔታ በሚያራቁቱበት የፋሽን ልብስ ይታበያሉ፤ ሌሎች ደግሞ ልክ በኢሳይያስ 3፡16-24 እንደ ተጠቀሰው፥ በሚንቃጨሉ የአንገትና የጆሮ ጌጣጌጦች፥ የእጅና የእግር አልቦዎች፥ ቀለበቶች፥ ወዘተ... ይኩራራሉ። የተቀሩትም «እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፤ ለትሑታን ግን ጸጋውን ይሰጣል» የሚለውን እየዘነጉ (1ኛ ጴጥ. 5፡5)፥ በቀደምት አባቶቻቸው፥ በብሔረሰባቸው፥ በባህላቸው፥ ወዘተ. ይታበያሉ። እግዚአብሔር ትዕቢትንና እብሪትን ይጠላል (ምሳሌ 8፡13)። «ትዕቢት ጥፋትን፥ ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል» (ምሳሌ 16፡18)።

2. ውሻው - የሥጋ መሻትን፥ ምግባረ-ብልሹነትን፥ ዝሙትን ያመለክታል። በዚህ ስፍራ የተጠቀሱ ኃጢአቶች በተለይ በአሁኑ የመጨረሻው ዘመን እጅግ በርክተው በመገኘታቸው፥ ኢየሱስ ከ2000 ዓመታት በፊት የመጨረሻው ዘመን እንደ ሰዶምና ገሞራ እንደሚሆን የተነበየው ተፈጻሚነት ስለማግኘቱ መቀበል ይኖርብናል። ይህ የኃጢአት መንገድ ወንዶችንና ሴቶችን አጥብቆ በመያዝ ወደ ሃይማኖተኛ ሰዎች ቤቶችና ተቋሞች፥ ትምህርት ቤቶችና ሆስቴሎች መዝለቅ ብቻ ሳይሆን፥ እጅግ በረቀቀና ኃፍረት በራቀው መልኩም፥ በሲኒማ፥ በቲያትር፥ በጸያፍ ሥነ-ጽሑፎችና በበርካታ ዘዴዎች በኩል ወደ ሰዎች

Copyright ANCP

ልብ ይገባል። በዚህም ዓይነት እግዚአብሔር ኃጢአት ብሎ የሚጠራው ነገር እንደ ዘመናዊ ምግባር ይታያል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶች የፍጹም ሕይወት አሳባቸውን ከሲኒማና ልብወለዶች መጻሕፍት በመመራት ይመሠርታሉ፤ ሆኖም ራሳቸውን ከመከራ፥ ከኃፍረትና ከጸጸት ውስጥ ይጥላሉ። ምግባረ-ብልሹና ልቅ ሕይወት የሚመሩ ወንድና ሴት ተዋንያን ለአዲሱ ትውልድ እንደ ጀግና ይታያሉ። የዳንስ ምሽቶችም ባመዛኙ የምግባረ-ብልሹነት መፈልፈያ ስፍራዎች ናቸው። እንደ ዮሴፍ (ዘፍ. 39) ዓይነት የእግዚአብሔር ጀግኖች በምሳሌነት አይወሰዱም። አመንዝራ ሴት ወይም ወንድ በሚያገኝበት ጊዜ በሞት ይቀጣ የነበረው የጥንቱ አረማዊ ጐሣ እንኳን «ሠለጠንኩ» የሚለውን ዘመናዊ ትውልዳችንን ሊያስተምርና በፍርድ ቀን ተነሥቶ ሊኮንነን ይችላል። እግዚአብሔር በምግባረ-ብልሹነታችን መቀጠሉን አቁመን በቀና መንገድ እንድንመላለስ ይነግረናል። «ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል። ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም» (1ኛ ቆሮ. 6፡18-19)። «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ» (1ኛ ቆሮ. 3፡17)።

3. አሳማው - የሆዳምነትና የስካርን ኃጢአት ያመለክታል። አሳማ የሚያገኘውን ማንኛውንም ቆሻሻም ሆነ ንጹሕ ነገር ከማግበስበስ የማይመለስ ቆሻሻ እንስሳ ሲሆን፥ ኃጢአተኛ ልብም እንደዚሁ ማንኛውንም በግድፈት የታጀበ አሳብ፥ አገላለጽ፥ ሥዕል፥ ሥነ-ጽሑፍ፥ ወዘተ. ወደ ውስጡ ያስገባል። የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንዲሆን የተፈጠረው ሰውነት፥ በጐጂ ምግቦች፥ ትምባሆ በማጤስና በመቃም፥ በጐጂ ዕፆችና

Copyright ANGP

ኪንኖች፥ ወዘተ... በመጠቀም ይረክሳል። የትምባሆና የዕፅ ሱስ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ወንዶችንና ሴቶችን ይዞአቸዋል። እነዚህን የትምባሆ ቁራኛዎችና የሰይጣን ባሪያዎች ነፃ ሊያወጣ የሚችለው የእግዚአብሔር ኃይል ብቻ ነው። አብዛኛዎቹ ወደ ሃይማኖት የሚያጋድሉ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ለማጤስ ባይደፍሩም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆነውን ሰውነታቸውን በዚህ እንደ ቆሻሻ ዐረም በሚቈጠር የገማ ጢስ ከመበከል ግን አይመለሱም። ሐዋርያው ጳውሎስ፡- «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል» (1ኛ ቆሮ. 3፡16፥ 17፤ 6፡18፥ 19) ብሏል።

ስግብግብ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ የሚሰጠው አይደለም። ለመኖር እንበላለን እንጂ ለመብላት አንኖርም። ረሃብ በቂ ምግብ በመብላት ሊረግብ ሲችል፥ ስግብግብነት ግን ሁልጊዜም «ስጠኝ! ስጠኝ!» እያለ ከመጮኽ አይመለስም።

ስግብግብነት ከቶውንም ሊጠግብና ሊሞላ አይችልም። በብሉይ ኪዳን ሕግ ሆዳምና ሰካራም ተወግረው እንዲሞቱ ታዞአል (ዘዳ. 21፡18-21)። «ሰካርና ሆዳም ይደኸያሉና፥ የእንቅልፍም ብዛት የተቦጫጨቀ ልብስ ያስለብሳልና» (ምሳሌ 23፡21)። ሆዳምና ለፍላጐቶቹ ባሪያ የሆነ አንድ ባለጠጋ በሞተ ጊዜ ራሱን በሲኦል ውስጥ እንዳገኘ ልብ በል። መቼም የመጠጥ ክፋት አንድ በአንድ መዘርዘር የሚያሻው አይደለም። የመጠጥን ጉዳይ በለዘብተኛነቱ መመልከት የታወቀ ጉዳይ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ግን ሰካራም የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርስ በግልጽ ይናገራል። ቢራም ምግብ ሳይሆን አእምሮን ግራ የሚያጋባና የሚጎዳ መጠጥ ስለሆነ የሚጠጡት ሰዎች የሞኝነትን ተግባር ይፈጽማሉ። በዚህም ምክንያት ምግባረ-ብልሹነት ይጫናቸውና እርስ-በርስ ይገዳደላሉ። ባይጠጡ ኖሮ ይህንን የመሰለ ተግባር ባልፈጸሙም ነበር። «የወይን

Copyright ANGP

ጠጅ ፌዘኛ ያደርጋል፤ ብርቱ መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል፤ በዚህም የሳተ ሁሉ ጠቢብ አይደለም» (ምሳሌ 20፥ 1)።

እነዚያ አስካሪ መጠጥ ሠርተው የሚሸጡ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት የጠጪዎቹን ያህል በደለኞች ናቸው። ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች እግዚአብሔር «የወይን ጠጅ ለመጠጣት ኃያላን የሚያሰክረውንም ለማደባለቅ ጨካኞች ለሆኑ ... ወዮላቸው!» ስለሚል (ኢሳ. 5፥22)። «ባልንጀራውን ለሚያጠጣው ... ለሚያሰክረውም ወዮለት!» (ዕንባ. 2፥15)። «ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም» (1ኛ ቆሮ. 6፥9፥ 10) ይላል።

የሰብአዊ ተፈጥሮአችን ኃጢአቶች የታወቁ ናቸው። ጥቂቶቹም ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡- «የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኩሰት፥ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም» (ገላ. 5፥19-21) «መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና» (ኤፌ. 5፥18)።

ኢየሱስ መንፈሳዊ ነገሮችን ለተጠማ ሰው ሁሉ የሚከተለውን ግብዣ ያቀርባል፡- «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ» (ዮሐ. 7፥37)። «እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ፥ ወደ ውኃ ኑ፥ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም፤ ኑ ያለ ገንዘብም ያለዋጋም [መንፈሳዊ] የወይን ጠጅና ወተት ግዙ» (ኢሳ. 55፥1)። «እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ

Copyright ANCP

የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ» (ዮሐ. 4፡ 14)።

4. ዔሊው - ስንፍናን፥ ለመታዘዝ መዘግየትንና ጥንቆላን ያመለክታል። «ዓመፀኛነት እንደ ምዋርተኛነት ኃጢአት ነው» (1ኛ ሳሙ. 15፡23)። «ታካችን ምኞቱ ትገድለዋለች፥ እጆቹ ይሠሩ ዘንድ አይፈቅዱምና። ... ቀኑን ሁሉ ምኞትን ይመኛል» (ምሳሌ 21፡25-26)። ሚካ ለእስራኤላውያን፥ «ተነሡ፥ በእነርሱ ላይ እንውጣ፤ እናንተ ዝም ትላላችሁን? ትሄዱ ዘንድ ምድሪቱንም ለመውረስ ትገቡ ዘንድ ቸል አትበሉ» ማለት አስፈልጎት ነበር (መሳ. 18፡9)። ሰብአዊ ተፈጥሮ በጣም ስንፍና ስለሚያጠቃው የእግዚአብሔርን ነገሮች ለመቀበል ይዘገያል። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡- «በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ» (ሉቃስ 13፡24)። «የሚፈልገውም ያገኛል» (ማቴ. 7፡8)። «መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፥ ግፈኞችም ይናጠቋታል» (ማቴ. 11፡ 12)።

Copyright ANCP

ለነፍሳችን ደኅንነትና መንፈሳዊ ዕድገት ግዴለሽ መሆን ወደ ዘላለማዊው ሞት ይመራል። ከመጸለይ፥ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች ከመፈለግና የእግዚአብሔርን የበለጸጉ የተስፋ ቃሎች ከመቀበል በማራቅ፥ ወደ ጥፋት ይመራል። እግዚአብሔር ልብህን ዛሬ እንድትሰጠው በማሳሰብ ሲናገርህ፥ ዲያብሎስ ደግሞ ነገ ወይም በሌላ ተስማሚ ቀን እንድታደርገው ያባብልሃል፤ የሚያሳዝነው ግን፥ ይህ ሌላ ቀን ጨርሶም ላይመጣ ስለሚችል፥ ደኅንነትን ሳታገኝ ያለ ክርስቶስ ትሞታለህ። እግዚአብሔር «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ... ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ» ይለናል (ዕብ. 3፡8፡9)። ደኅንነትን ላላገኙት ሌላ ቀን በማስተላለፍ ስንቶች ለመንፈሳዊ ሞት ተዳርገዋል? የነገው ዕለት ያንተ አይደለም!

የዔሊ ቅርፊት ባመዛኙ ጠንቋዮች ለጥንቈላ ተግባር የሚጠቀሙበት ሲሆን፥ በዚህም ስፍራ የሚያመለክተው ሕያውን አምላክ በመተማመን ፈንታ ጥንቈላን፥ ኰከብ ቈጠራን ወይም

ምትሐታዊ ልምምድን ማድረግና ማመን ከባድ ኃጢአት መሆኑን ነው። በተለይም በፈተናና በሕመም፥ በመከራና በኃዘን ጊዜ፥ በመልካም ወይም በክፉ ዕድል ከማመን ይልቅ ሊረዳን የተዘጋጀውን ሕያው አምላክን እንድንጠራ ተነግሮናል፡- «የሰው አካሄድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይጸናል» [መዝ. (37)፡23]። «ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል። እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፥ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ» (ያዕ. 5፡14-16)። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን «ወንድ ልጁን ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ፥ ምዋርተኛም፥ ሞራ ገላጭም፥ አስማተኛም፥ መተተኛም፥ በድግምት የሚጠነቁልም፥ መናፍስትንም የሚጠራ፥ ጠንቋይም፥ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው» (ዘዳ. 18፡10-12) በማለት ያዛቸዋል። «ውሻዎችና አስማተኞች ሴሰኞችም ነፍሰ ገዳዮችም ጣዖትን የሚያመልኩ ውሸትንም የሚወዱና የሚያደርጉ ሁሉ በውጭ አሉ» (ራእይ 22፡15)።

«ወደ መናፍስት ጠሪዎችና ወደ ጠንቋዮች አትሂዱ፤ እንዳትረከሱባቸውም አትፈልጉአቸው፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ» (ዘሌ. 19፡31)። «እነርሱም፡- የሚጮኹትንና ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው የሚናገሩትን መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ጠይቁ ባሉአችሁ ጊዜ፥ ሕዝቡ ከአምላኩ መጠየቅ አይገባውምን? ወይስ ለሕያዋን ሲሉ ሙታንን ይጠይቃሉን?» (ኢሳ. 8፡19-20)።

ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ ስታነብ ሳለህ፥ እግዚአብሔር ከኃጢአትህ ተመልሰህ ሕይወትህን እንድትሰጠው እየተናገረህ ነው፤ በልብህ ውስጥ የተቀመጠው የዔሊ መንፈስ ግን ከዚህ ውሳኔ

Copyright ANGP

ላይ እንዳትደርስ የተለያዩ የመደለያ አሳቦች በማቅረብ ያሰናክልሃል - ልብህንም በፍርሃት ለማሸበር ይጣጣራል። «እውነተኛ ክርስቲያን ሆኜ ከተለወጥሁ፥ ቤተሰቦቼ፥ ወዳጆቼና ሌሎች ሰዎች ምን ይሉኛ ይሆን? በዳንስ ጭፈራዎች፥ ፓርቲዎችና ሌሎችም ዓለማዊ መዝናኛዎች ላይ መገኘቴን ባቆም ምን ይከተል ይሆን?» ስትል ሥጋት ይገባሃል። ሰውንና ሞትን መፍራት የዲያብሎስ ባሪያ አድርጎ ስለሚያስገዛህ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘውን ታላቅ ባለጸግነት፥ ድንቅ ሰላም፥ በቃላት ሊገለጽ የማይችለውን ደስታ፥ ክብሩን፥ በሐሤት የተሞላውን ዘላለማዊ ሕይወት ለመመልከት ያዳግትሃል። በምትኩ፥ ክርስቶስ ወደ ልብህ እንዲገባ በምትፈቅድበት ጊዜ የምታጣቸውን ወይም የምታቆማቸውን ነገሮች ማየት ትጀምራለህ። ይሁንና ክርስቶስ ሞትን በመፍራታቸው ምክንያት፥ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በባርነት ቀንበር ሥር ሲማቀቁ የነበሩትን ሰዎች ነፃ ለማውጣት መምጣቱን ዛሬውኑ ልብ በል (ዕብ. 2፡14፥ 15)። አለበለዚያ ግን ለመታዘዝ የመዘግየት መንፈስ እየተጠናወተህ በሄደ መጠን፥ ልብህን እንደ ዔሊ ቅርፊት እያጠጠረውና እያደነደነው እንደሚሄድ አትዘንጋ።

5. ነብር - በጣም ኃይለኛና ጨካኝ አውሬ ነው። ጥላቻ፥ ቁጣና ንዴት ብዙውን ጊዜ የሰውን ልብ በመግዛት፥ ወደ ነፍስ ማጥፋት ይመራሉ። ለጊዜው ንዴትህን ለመቆጣጠር ትችል ይሆናል። በኋላ ግን ንዴትህ ጦፎ ይወጣል። ይህ ደካማነት በልብህ ውስጥ እንዳለ መቀበልና ኢየሱስ ነፃ እንዲያወጣህ መጠየቁ ጥበብ ነው። «ከቁጣ ራቅ መዓትንም ተው» [መዝ. (37)፡8]። «ቁጣ ምሕረት የሌለው ነው» (ምሳሌ 27፡4)። «በነፍስህ ለቁጣ ችኩል አትሁን ቁጣ በሰነፍ ብብት ያርፋልና» (መክ. 7፡9)። «ቁጣን ... አስወግዱ» (ቈላ. 3፡8)።

ብዙ ፈሪዎች አንዳንድ ክፉ ድርጊቶችን ወይም በቀሎችን ለመፈጸም በመጠጥ ኃይል ይደፋፈራሉ፤ ይኼ ግን «የእባብ መርዝ፥ የእፉኝትም ሥራ ነው» (ዘዳ. 32፡33)። በቀል

Copyright ANGP

ለኃጢአተኛ ልብ ጣፋጭ ተግባር ሲሆን፥ በደልን ሁሉ የሚቀጣው ግን እግዚአብሔር ነው። ኢየሱስ፥ «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» (ማር. 12፡31)፥ እንዲሁም «ጠላቶቻችሁን ውደዱ» (ማቴ. 5፡44) ብሎአል።እግዚአብሔር በተጨማሪም ሌሎች የፈጸሙብንን በደል ይቅር ብንል፥ በደላችንን ይቅር እንደሚል የተስፋ ቃል ገብቶልናል (ማቴ. 6፡12)። የመኮራረፍና የማጉረምረም መንፈስ በእግዚአብሔር የተጠላ ነው። ደም ለማፍሰስና ጦርነት ለመክፈት የሚነሣሣው ክፉ ፍላጐት የሚመነጨው ከሰው ልብ ስለሆነ፥ ይህንን ለዘለቄታው ለማስወገድ ከተፈለገ በልብ ውስጥ እውነተኛ ሰላም ሊመሠረት ይገባዋል።

6. አባብ - ሔዋንን በዔድን ገነት በማታለል ከእግዚአብሔር ጋር የነበራትን ጣፋጭ ኅብረትና ወዳጅነት አበላሽቷል። ሰይጣን አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር በፍጹም ኅብረት እየኖሩ፥ የእርሱን ስፍራ ወስደው ዓለምን ሲገዙ ሲያይ ከፍተኛ ቅንዓት አደረበት። ከዚህም የተነሣ፥ ሊያጠፋቸው ዕቅድ ነደፈ። ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን አስደናቂ ወዳጅነትና ሕይወት በማደፍረስም ዕቅዱ ተሳክቶለታል። ይህም ዲያብሎሳዊ ቅንዓትና ምቀኝነት በሰዎች ልብ እያደረ፥ ሌሎች በደስታና በምቾት እንደሚኖሩ በሚመለከቱበት ጊዜ የቅንዓት ስሜት ይጠናወታቸውና ደስታን ያጣሉ። ቅንዓት የሌሎችን ደስታ ለማክተም ወደ ቀናተኛው ልብ ክፉ አሳቦችን የሚያመጣ ሲሆን፥ ይህም ወደ ሞት እስከሚመራ ድረስ የበረታ ሊሆን ይችላል። ይህ በተለይ በአንዳንድ የጋብቻ ሕይወት ውስጥ የሚከሰት ነው። «ቅንዓት ለሰው የቁጣ ትኩሳት ነውና፥ በበቀልም ቀን አይራራለትምና» (ምሳሌ 6፡34)። ቅንዓት፥ በንግድም ሆነ በሌሎችም የሕይወት መስኮች ውስጥ የማይነገር ሥቃይና ጥላቻ ያስከትላል። ክርስቲያን ሠራተኞች፥ ሰባኪያንና አገልጋዮች እንኳ እግዚአብሔር በሌሎች ባሪያዎቹ ከእነርሱ በላይ እንደሚጠቀምባቸው ሲመለከቱ በዚህ በቅንዓት ኃጢአት

Copyright ANGP

ሊጠቁ ይችላሉ። ስለሆነም፥ ባለማቋረጥ ልባቸውን ሊጠብቁና እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ባፈሰሰልን ንጹሕ ፍቅር ሊሞሉ ይገባል (ሮሜ 5፡5)፤ ይህ ካልሆነ ግን ለእግዚአብሔር የሚኖራቸው ጠቀሜታና አገልግሎት በቅንዓት ተፈጥሮ ይበላሻል።

7. እንቁራሪት - በዚህ ስፍራ ስግብግብነትንና የክፋት ሁሉ ሥር የሆነውን ገንዘብ የመውደድ ኃጢአት ያመለክታል (1ኛ ጢሞ. 6፡10)። በኮንጎ ውስጥ የተወሰኑ እንቁራሪቶች በቁንጣን ፈንድተው እስኪሞቱ ድረስ በመቶ የሚቆጠሩ ጉንዳኖችን ሲበሉ ታይተዋል። ስግብግብ ሰው ድህና ችግረኛውን ለመርዳት እጁን ለመዘርጋት አይፈልግም፤ ዳሩ ግን ታማኝነት በሚታይበትም ሆነ ታማኝነት በጐደለው መንገድ፥ በሚችለው በማንኛውም ዘዴ ሁሉ ተጠቅሞ የዚህን ዓለም ብልጽግና ለማካበት ይፈልጋል። ኢየሱስ ራሱ፡- «ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቈፍረው በሚሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቈፍረው በማይሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና» (ማቴ. 6፡19-21) ብሏል። ወርቅ፥ ብርና ልብሶችን በመውደዱ፥ አካንና ቤተሰቡ በድንጋይ ተወግረው ሞተዋል (ኢያሱ 7)። የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የነበረው የአስቆሮቱ ይሁዳ የገንዘብ ፍቅር ጌታውንና አምላኩን አሳልፎ እንዲሰጥ ስላደረገው ራሱን ሰቅሎ ሞቷል። ክፋቱ ያለው ከገንዘቡ ወይም ከወርቁ ላይ ሳይሆን በሰው ልብ ውስጥ ተሰውሮ በሚቀመጠው የገንዘብ ፍቅር ነው።

ከሁሉም መደቦችና የዘር ሐረጐች የተውጣጡ በሺህ የሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች፥ በቁማርና በውርርድ በመሸነፍና በማሸነፍ አማካኝነት እጅግ ታላቅና ቅጽበታዊ ብልጽግና ለማግኘት ካላቸው አደገኛ ፍላጐት የተነሣ፥ የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ሕይወት

ያበላሻሉ። ብዙ ሳይደክሙ በአቋራጭ መንገድ ለመክበር የሚደረገውም ጥረት ወደ ስርቆት፥ ነፍስ ግድያና የራስን ሕይወት ወደ ማጥፋት ያመራል። የገንዘብ ፍቅርና ስግብግብነት፥ የዝናና የሥልጣን ፍቅርን የመሳሰሉ በርካታ አጃቢዎች አሉት። ይህም ሥልጣን፥ በሌሎች ላይ ለመግዛት የሚያበቃ የፖለቲካ ሥልጣን፥ ድህን ለመጨቆን የሚያስችል የገንዘብ ኃይል፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለአንድ የቤተ ክርስቲያን ድርጅት ስም በመቆርቆር የነርሱ ቤተ ክርስቲያን አባል ሳይሆን ክርስቶስን ለመከተል የሚፈልጉትን ሰዎች ለማጥላላት የሚያገለግል ሃይማኖታዊ ሥልጣን ሊሆን ይችላል (ማር. 9፡38)። ኢየሱስ፡- «የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፥ ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ» ብሏል (ሉቃስ 12፡15)። የሀብታሙ ሰው ታሪክ እንዲህ ተተርኮአል፡- «አንድ ባለጠጋ ሰው እርሻ እጅግ ፍሬያማ ሆነችለት። እርሱም፡- ፍሬዬን የማከማችበት ስፍራ አጥቻለሁና ምን ላድርግ? ብሎ በልቡ አሰበ። እንዲህ አደርጋለሁ፤ ጐተራዬን አፍርሼ ሌላ የሚበልጥ እሠራለሁ፥ በዚያም ፍሬዬንና በረከቴን ሁሉ አከማቻለሁ፤ ነፍሴንም፡- አንቺ ነፍሴ፥ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፤ ዕረፊ፥ ብዪ፥ ጠጪ፥ ደስ ይበልሽ እላታለሁ። እግዚአብሔር ግን፡- አንተ ሰነፍ፥ በዚች ሌሊት ነፍስህን ካንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል፤ ይህስ የሰበሰብኸው ለማን ይሆናል? አለው። ለራሱ ገንዘብ የሚያከማች፥ በእግዚአብሔር ዘንድም ባለጠጋ ያልሆነ እንዲህ ነው» (ሉቃስ 12፡16-21)። «ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?» (ማር. 8፡36)። «ለነፍሳችሁ በምትበሉት ወይም ለሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ ... ዳሩ ግን መንግሥቱን ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።... መዝገባችሁ ባለበት ልባችሁ ደግሞ በዚያ ይሆናልና» (ሉቃስ 12፡22-34)።

8. ሰይጣን - የውሸቶች ሁሉና ውሸትን የሚናገሩት ሰዎች ሁሉ አባት፥ ወደ ኃጢአት የመራን የልብ ገዥ ነው «እናንተ

Copyright ANGP

ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና» (ዮሐ. 8፡44)። ትንሽ ውሸት የትልቅ ውሸትን ያህል የከፋ ነው። የሚነገሩ፥ የሚጻፉና በተግባር የሚተረጐሙ ውሸቶች አሉ። ግብዝ ሰው በእውነት ያልሆነውን ለመሆን ስለሚሞክር ውሸተኛ ነው። እግዚአብሔር ሊዋሽ አይችልም፤ ክርስቲያንም እንዲሁ (ቲቶ 1፡2)። «ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል፥ በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም» (1ኛ ዮሐ. 1፡6)። «ውሻዎችና አስማተኞዎች ሴሰኞዎችም ነፍሰ ገዳዮችም ጣዖትንም የሚያመልኩት ውሸትንም የሚወዱና የሚያደርጉ ሁሉ በውጭ አሉ» (ራእይ 22፡15)። «በሐሰት የሚናገር ሐሰተኛ ምስክር» በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው (ምሳሌ 6፡19)።

9. ኮከብ - በሰው ሁሉ ውስጥ የሚኖረውን ሕሊና ያሳያል። በዚህ ሥዕል ላይ የሚወከለው ግን ክፋትንና በኃጢአት መጨማለቅን ነው። ምናልባትም ከተፈጸመ ኃጢአት የተነሣ የሞተ፥ የቆሸሸና የከፋ ለመሆን በቅቶ ይሆናል። የታወረና በኃጢአት የተበከለ እንደመሆኑም የራሱን ተግባራት በትክክል ሊዳኝ አይችልም። ይህ ዓይነቱ ዓመፀኛ ሕሊና አንዳንድ ጊዜ ዝም ያለ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ በመከራ የተጨነቀ ሊሆን ይችላል። ይቅር ማለት ሲገባው ይወቅሳል፤ መውቀስ ሲገባው ይቅር ይላል። እምነትን በመተው፥ ውሸተኛ መናፍስትን በመታዘዝና የአጋንንትን ትምህርቶች በመከተል፥ ብሎም በአታላይ ውሸተኞች የሚሰራጩትን ትምህርቶች በማድመጥ ሊደነዝዝና በጋለ ብረት እንደተተኮሰ ሁሉ ሞት ሊያንዣብብበት ይችላል (1ኛ ጢሞ. 4፡1፥ 2፤ ዕብ. 10፡22)።

Copyright ANGP

10. ዓይን - የእግዚአብሔር ዓይን በሰው ልብ ውስጥ የሚሆነውን ሁሉ ይመለከታል። መቼም ከነበልባልማ ዓይኖቹ ፊት የሚሰወር ነገር የለምና የልብን ድብቅ አሳቦችና ፍላጐቶች ሳይቀር ይመለከታል። ክፉ ተግባራትን እጅግ ጽልመት በጠላበት ሌሊት፥ ጥቅጥቅ ባለደን፥ ጥልቅ በሆነ ጉድጓድ ወይም በፈለግህበት ሰዋራ ስፍራ ብታከናውንም ከእግዚአብሔር ዓይኖች ግን ልትሰውረው አትችልም። (በነዚህ በእያንዳንዱ ሥዕሎች ላይ የቀረበው የዓይን አገላለጥ፥ በሰውየው ፊት ላይ ከሚነበበው ስሜት ጋር እንዴት እንደሚስማማ ልብ በል)።

11. ትናንሽ የእሳት ምላሶች - እነዚህ በልቡ ምስል ዙሪያ የሚገኙት የእሳት ምላሶች ኃጢአተኛውን ልብ የሚጋርደውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ያሳያል። እግዚአብሔር ኃጢአትን ቢጠላም፥ ኃጢአተኛውን ይወዳል። የኃጢያተኛውን ሞት አይፈልግም፤ ይልቁንም ከኃጢአቶቹ ተመልሶ በሕይወት እንዲኖር ይፈልጋል (2ኛ ጴጥ. 3፡9)። ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው ኃጢአተኞችን ለማዳን ሲሆን፥ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ ምክንያት በሰማይ ታላቅ ደስታ ይሆናል (ሉቃ. 15፡7)። በተጨማሪም፥ ትናንሾቹ የእሳት ምላሶች የኢየሱስ ክርስቶስንም ደም ያሳያሉ፤ «የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐ. 1፡29)።

12. መልአክ - የእግዚአብሔርን ቃል ይወክላል። እግዚአብሔር፥ በሰይጣን ተታለው ከባድ የኃጢአት ጭነት ተሸክመው ለሚኖሩ ሰዎች ለመናገር ይፈልጋል፤ ይህንንም የሚያደርገው ከኃጢአተኛ መንገዳቸው ተመልሰው የእግዚአብሔርን ብርሃንና ፍቅር ወደ ልባቸው እንዲያስገቡ ነው።


13. ርግብ - የመንፈስ ቅዱስ አምሳል ስትሆን፥ ስለ እግዚአብሔር እውነቱን የሚገልጸው፥ ኃጢአትና ጽድቅ የሆነውን የሚያሳየው፥ እንዲሁም ስለ እግዚአብሔር ፍርድ የሚናገረውም ይኸው መንፈስ ቅዱስ ነው (ዮሐ. 15፡26)። በዚህ ሥዕል ላይ

Copyright ANGP

መንፈስ ቅዱስ ከሰው ልብ በስተውጭ መሆኑ ተመልክቷል፤ ይኸውም ኃጢአት በሚገዛበት ልብ ውስጥ ሊኖር ስለማይችል ነው።

የዚህ ልብ ሥዕል ከራስህ ልብ ጋር የሚመሳሰል ከሆነ፥ ወደ እግዚአብሔር በመጥራትና ልብህን ለእርሱ በመክፈት የቃሉ ብርሃን በልብህ እንዲያበራ ፍቀድ። «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ» (የሐዋ. 16፡31)። እግዚአብሔር ልብህን እንደሚለውጥ፥ አዲስ ልብና አእምሮ እንደሚሰጥህ የተስፋ ቃል ገብቶልሃል (ሕዝ. 11፡19)። ይህም በሁለተኛው ሥዕል ውስጥ ተብራርቷል።

Copyright ANGP




2. ኃጢአተኛነቱን ያመነ ልብ

## ሁለተኛው ሥዕል

ይህ ሥዕል ኃጢአተኛነቱን አምኖ ንስሐ በመግባት፥ እግዚአብሔርን መፈለግ የጀመረን ልብ ያሳያል። መልአኩ የእግዚአብሔርን ቃል ይዞአል፤ «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል» (ዕብ. 4፡12)። የእግዚአብሔር ቃል የኃጢአት ተገቢ ደመወዙ ሞት ነው (ሮሜ 6፡23) እና ሰው ሁሉ አንድ ጊዜ ከሞተ በኋላ ፍርድ እንደተመደበበት ያስታውሰናል (ዕብ. 9፡27)። የኃጢአተኛና የማያምን ሰው ስፍራ በዲንና በእሳት የሚቃጠል ባሕር ይሆናል (ራእይ 21፡8)።

## ኃጢአተኛነቱን ያመነ ልብ


መልአኩ በሌላኛው እጁ የሰው ራስ ቅል ይዞአል። ይህም ለሁላችንም ሞት እንደማይቀርልን ለኃጢአተኛው ለማስታወስ ነው። በምንሳሳለት ገላችን፥ እንዲሁም መሻቱን ለማርካት የምንሰበስበው ልብስ፥ ምግብና ፍላጐቶች ሁሉ አንድ ቀን ወደ ብስባሽነት ይለወጣሉ፤ ትልም ይበላቸዋል። ነፍሳችንና መንፈሳችን ግን ለዘላለም የሚኖሩ ሲሆን፥ አንድ ቀን ለፍርድ በክርስቶስ ፊት ይቀርባሉ (2ኛ ቆሮ. 5፡10)።

በዚህ ስፍራ ኃጢአተኛው የእግዚአብሔርን መልእክት ማስተዋልና ለእግዚአብሔር ፍቅር ልቡን መክፈት ሲጀምር እንመለከታለን። መንፈስ ቅዱስ በጨለማና ኃጢአት በበረከተበት ልብ ውስጥ ብርሃኑን መርጨት ይጀምራል። የእግዚአብሔርም ብርሃን ጨለማን ሁሉ ከዚህ ልብ ውስጥ ለማስወገድ ይመጣል። የእግዚአብሔር ብርሃን ሲገባ፥ ጨለማ ስፍራውን መልቀቅ አለበት። በተለያዩ አውሬዎች የተመሰለው ኃጢአትም መወገድ አለበት። ስለሆነም፥ አንተም ውድ አንባቢያችን የዓለም ብርሃን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ልብህ እንዲገባ ፍቀድለት፤ በዚህም ሥዕል

Copyright ANCP

እንደተመለከተው ጨለማና የከፋት የጨለማ ውጤቶች ከልብህ ለቀው ይወጣሉ። ኢየሱስ፡- «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም» ብሏል (ዮሐ. 8፡12)። በራስህ ጥረት፥ በራስህ ወይም በሌሎች ሰዎች ጥበብ ኃጢአትን ከልብህ ለማውጣት የምታደርገው ትግል ሊሳካልህ አይችልም። ከሁሉም በላይ ቀላሉና አስተማማኙ፥ ፈጣኑና ስኬታማ ብሎም ብቸኛው መንገድ፥ ብርሃን የሆነውን ኢየሱስን ማስገባትና ኃጢአት የሆነውን ጨለማ ማስወጣት ነው። ጨለማ በነገሠበት ሌሊት፥ ጨረቃና ከዋክብት የተወሰነ እገዛ ሊያደርጉልን ቢችሉም፥ ፀሐይ ስትወጣ ግን ጨለማውም ሆነ አናሳ ብርሃናት ስፍራቸውን ይለቃሉ። ኢየሱስ የጽድቅ ፀሐይ ነው። በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ቤተ መቅደስ በሄደ ጊዜ፥ በዚያ የሚገዙትንና የሚሸጡትን ሁሉ አባረረ። «ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል፥ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት» በማለት የገንዘብ ለዋጮችን ገበታዎችና የርግብ ሻጮችን ወንበሮች ገለበጠ (ማቴ. 21፡13)። ልብህ የተፈጠረው የእግዚአብሔር ቤት፥ የእግዚአብሔር መቅደስ እንዲሆን ነው። እግዚአብሔር በልብህ ውስጥ ሊኖር፥ ሊያስውበው፥ በብርሃን፥ በፍቅርና በደስታ ሊሞላው ይፈልጋል። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ለኃጢአታችን ይቅርታ ለመስጠት ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ከኃጢአት ኃይልና አገዛዝም ነፃ ሊያወጣን ነው። «እንግዲህ ልጁ (ኢየሱስ) አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ» (ዮሐ. 8፡36)።

Copyright ANGP




3. ንስሐ የሚገባ ልብ

## ሦስተኛው ሥዕል

ይህ ሥዕል እውነተኛ ንስሐ ለመግባት የተነሣውን ኃጢአተኛ ሰው የልብ ሁኔታ ያሳየናል። አሁን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞተባቸው በርካታ ኃጢአቶቹ ምን ያህል ታላቅና የከፉ እንደሆኑ ያመለክታል። የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መልአክ የያዘውን መስቀል በሚያይበት ጊዜም በኃዘን የተነካው ልቡ ይበልጥ ይሰበርና ስለ በርካታ ኃጢአቶቹም የጠለቀና ከልብ የመነጨ ጸጸት ያድርበታል። በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ታላቅ ፍቅር በሚመለከትበት ጊዜ በዚህ ፍቅሩ ልቡ ይቀልጣል፤ በተለይም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በእርሱ ምትክ በመስቀል ላይ በመሞት፥ በርካታ ኃጢአቶቹን ለማስወገድ ፈቃደኛ ሆኖ ወደዚህች ዓለም መምጣቱን ሲገነዘብ፥ ልቡ በፍቅሩ ይነካል።

የኢየሱስ መገረፍ፥ በእሾህ አክሊል መቊሰል፥ በእጆቹና በእግሮቹ ምስማሮች ተቸንክረውበት ለኃጢአታችን በመስቀል ላይ መሞቱ፥ ሙሉ ለሙሉ ልቡንና ሕይወቱን በመለወጥ ንስሐ ለሚገባው ኃጢአተኛ በግልጽ ይታየዋል። በመስተዋት የሚያየውን ያህል ራሱን የሚመለከትበትን የእግዚአብሔርን ቃል በሚያነብበት ጊዜ፥ ከእግዚአብሔር ምን ያህል እንደራቀና ትእዛዛቱን እንደተላለፈ በበለጠ እየተረዳ ይመጣል። በከፍተኛ የኃዘንና የቊጭት ስሜት ዝሎ፥ በእንባና በመራራ ለቅሶ ልቡን በእግዚአብሔር ፊት ሲያፈስ፥ ኢየሱስ ወደርሱ በበለጠ ይቀርባል። «የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል» የሚለውን እውነት እየተረዳ ሲመጣ (1ኛ ዮሐ. 1፡7)፥ የእግዚአብሔር ፍቅርና ሰላም ወደ ልቡ መግባት ይጀምራል። «አቤቱ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ» [መዝ. (51)፡ 10]። እንዲሁም፥ የእግዚአብሔር ቃል፥ «ወደዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ» ይላል (ኢሳ. 66፡2)።

Copyright ANGP

መንፈስ ቅዱስም የኢየሱስን ቃላት ግልጽ ያደርግለታል፡- «አንተ (አንቺ) ልጅ አይዞህ፥ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ(ሽ)» (ማቴ. 9፡2)። አሁንም መስቀሉንና በመስቀል ላይ የፈሰሰውን የኢየሱስ ደም ሲመለከት፥ ይህ ሁሉ ለርሱ እንደተደረገ በማመን፥ የኃጢአት ሸክሙ እንደተወገደለት ይገነዘባል። ኢየሱስ እኛ ልንቀበለው የሚገባውን መከራ ተቀብሏልና፡- «ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ» (ኢሳ. 53፡5)።

መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር ፍቅር የነጻውን ልብ ይቆጣጠራሉ። በኢየሱስ ክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ፥ ለኃጢአቶቹ ይቅርታ እንደተደረገለት ይገነዘብና የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው የኢየሱስ ደም ከኃጢአት ሁሉ እንዳነጻው የሚያረጋግጥ ዋስትና ያገኛል (1ኛ ዮሐ. 1፡7)። በዚህም ጊዜ፥ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንደሚኖረው እንጂ፥ መንፈሳዊ ሞት እንደማይገጥመው እርግጠኛ ይሆናል (ዮሐ. 3፡16)። «በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት» (ኤፌ. 1፡7)። አሁን የሰብአዊ ተፈጥሮ ኃጢአታዊ ፍላጐት ስፍራውን በመልቀቅ፥ ለእግዚአብሔር በመኖርና «መጀመሪያ የወደደንን» አምላክ በማገልገል ጥልቅ መሻት ይተካል (1ኛ ዮሐ. 4፡19)። ዓለምንና የዓለምን ነገሮች ከመውደድ ይልቅ፥ እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ነገሮች ያፈቅራል።

በመሆኑም ምንም እንኳን ከዚህ ሥዕል እንደምንረዳው፥ ሰይጣን ወደኋላ ዞሮ እየተመለከተና ብሎም የሚገባበትን ቀዳዳ በመፈለግ ወደ ቀድሞ ቤቱ ለመመለስ ቢመኝም፥ ዳሩ ግን ኃጢአትን የሚወክሉት እንስሳት ከልቡ ውስጥ ተባርረዋል። ለዚህም ነው ኢየሱስ ዲያብሎስን ለመቃወም ነቅተን እንድንጸልይ የሚያስጠነቅቀን፤ በዚህም ጊዜ ከኛ ይሸሻል (ያዕ. 4፡7)።

Copyright ANCP

# አራተኛው ሥዕል

ይህ ሥዕል አዳኛችንና ጌታችን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት አማካኝነት ፍጹም ሰላምና ዘላለማዊ ደኅንነት ያገኘውንና «ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ» የሚለውን ክርስቲያን ያመለክታል (ገላ. 6፥14)። «ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር» ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞተ (1ኛ ጴጥ. 2፥24)፤ ክርስቲያን ለዓለም ሙት ነው። «በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ» ተብለን ታዘናል (ገላ. 5፥16፥ 25)።


ሌላው በልቡ ሥዕል ውስጥ የምንመለከተው ምስል የኢየሱስን ልብስ ካወለቁ በኋላ የታሰረበትን ግንድና በጭካኔ ጀርባውን የገረፉበትን ጅራፍ ነው። እርሱ ለኃጢአታችን ተቀጣ፥ «በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን» (ኢሳ. 53፥5)። ሄሮድስና ወታደሮቹ የተሳለቁበት ሲሆን፥ ከገረፉት በኋላ በራሱ ላይ በወርቅ አክሊል ምትክ የሾህ አክሊል ጫኑበት፤ በበትረ መንግሥትም ፈንታ በቀኝ እጁ የእንጨት ዘንግ አስጨብጠው ከፊቱ ተንበርክከው፡- «የአይሁድ ንጉሥ ሺህ ዓመት ንገሥ!» እያሉ አፌዙበት፤ ተፉበት፤ ራሱንም በበትር መቱት። እጅግ በሚያሳፍርና ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን ሲሳለቁበት ቆይተው፥ ሰቀሉት (ማቴ. 27፥27-31)።

የሚያሳዝነው፡- ዛሬም ቢሆን እየጸለዩ፥ በቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ላይ ተካፋይ እየሆኑና የእግዚአብሔርን ስም የሚያወድሱትን መዝሙሮች እየዘመሩ፥ ዳሩ ግን በኃጢአታዊ ተግባሮቻቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ባለማቋረጥ የሚሰቅሉ አንዳድ ስመ-ክርስቲያኖች አሉ (ዕብ. 6፥6)። «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» (ማቴ. 7፥21-27)።

Copyright ANGP

ሌላው በዚህ ሥዕል ውስጥ የሚገኘው ምስል የገንዘብ ፍቅር ልቡን በመያዙና ሊያስብ የሚችለውም ስለዚሁ የገንዘብ ጉዳይ ብቻ በመሆኑ፥ ጌታ ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠውና በሠላሳ ብር የሸጠው የይሁዳ ንብረት የሆነው የገንዘብ ከረጢት ነው። ችቦ፥ ሰንሰለቶች፥ ወዘተ. በምሽት ኢየሱስን አስረው የወሰዱት ወታደሮች የተገለገሉባቸው ናቸው። በመሠረቱ የቁማር መጫወቻ በሆነው የዕጣ መጣጣያ ሰዴቃ ልብሱን ለመከፋፈል ተገልግለውበታል። «ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ» [መዝ. (22)፡ 18]። የኢየሱስ የሆነውን ሁሉ ከወሰዱ በኋላ፥ ራሱን ግን «ይህ ሰው ንጉሣችን እንዲሆን አንፈልግም» በማለት አገለሉት።

Copyright ANGP




4. ከክርስቶስ ጋር መሞት

በአጠቃላይ ሰዎች በረከቶችን ሁሉ፥ ዝናብን ሁሉና የፀሐይን ብርሃን በሙሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመቀበል ይፈልጉ እንጂ፥ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እንደ ጌታቸውና አምላካቸው ሊያገለግሉት ግን አይፈልጉም። ብዙዎቹ እግዚአብሔርን የሚፈልጉት በመከራና በጭንቀታቸው ጊዜ እንዲረዳቸው ብቻ ነው።

«ከጭፍሮቹ አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ» (ዮሐ. 19፡33-37)። ዶሮ ከመጮኹ በፊት፥ ጴጥሮስ ኢየሱስን እንደማያውቀው በመግለጽ ሦስት ጊዜ ክዶታል፤ በኋላ ግን በመራራ ለቅሶ ንስሐ ገብቷል (ማቴ. 26፡69-75)። አንተስ ልብህን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደሰጠህ በግልጽ ታውጃለህ ወይስ ይህንን ለሌሎች ለመግለጽ ታፍራለህ? ኢየሱስ፡- «በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ» ብሏል (ማቴ. 10፡32-33)።

ኢየሱስ ከዚህ በተጨማሪም፡- «መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም» ብሏል (ማቴ. 10፡38)። በዓለቱ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ጥላ ሥር የሚጠለሉ ብፁዓን ናቸው!

የዘመናት ዓለት መሸሸጊያ

እፎይ ልበል ተጠልዬ ባንተ ጉያ፤

ከጐንህ የፈሰሰው የደም የውኃ ፏፏቴ፥

ምንጊዜም ትዝ ይለኛል እየታየኝ ከፊቴ፤

ኃጢአቴን ይጠበው፤

በደሌን ያርቀው።


Copyright ANCP

# አምስተኛው ሥዕል

ይህ ሥዕል በእግዚአብሔር የተትረፈረፈ ጸጋና ምሕረት የዳነውን ንጹሕና ጽዱ የኃጢአተኛ ሰው ልብ ያሳያል። ኢየሱስ ክርስቶስ የተስፋ ቃል እንደሰጠው፥ ይህ ልብ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቤተ መቅደስ፥ የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆኖአል። «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን» (ዮሐ. 14፡23)። እግዚአብሔር ሰውን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ይባርካል፤ ያከብራል፤ ከፍም ያደርጋል (ሉቃስ 1፡52)።

ልብ አሁን እውነተኛ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሆኖአል። ኃጢአት ተወግዶአል። የውሸት አባት በሆነው ሰይጣን ቁጥጥር ሥር ባሉት የተለያዩ እንስሳት ምትክ አሁን የእውነት መንፈስ የሆነው መንፈስ ቅዱስ በልብ ውስጥ አድሮ እናያለን። የኃጢአት መራቢያ በመሆን ፈንታ ያ ልብ አሁን ለሰውም ሆነ ለእግዚአብሔር አስደሳችና ተቀባይነት ያለውን የመንፈስ ፍሬ ማለትም ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትሕትና፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ ታማኝነት፥ ራስን መግዛትና የመሳሰሉትን በማፍራት፥ ውብ ፍሬ አምራች ዛፍ ወይም የአትክልት ስፍራ ሆኗል (ገላ. 5፡22-23)። አሁን የእውነተኛው ወይን ማለትም የኢየሱስ ክርስቶስ ፍሬ አምራች (አፍሪ) ዛፍ ሆኗል። የዚህ ፍሬ የማፍራቱ ምሥጢር እርሱ ከክርስቶስ ጋር ተጣምሮ መቆየቱና ክርስቶስና ቃሉ በርሱ መኖራቸው ነው (ዮሐ. 15፡1-10)።

Copyright ANGP




5. የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ

በመንፈስ ቅዱስ በመጠመቁና በመሞላቱም፥ ሰብአዊ መሻትንና ምኞቶቹን ለማሸነፍና ለመግደል የሚያበቃውን ኃይል ያገኛል (ገላ. 5፡24)። ሕይወቱም በመንፈስ ቅዱስ ስለሚመራ፥ ለሥጋዊና ለሰብአዊ ተፈጥሮ ምኞቶች አይሸነፍም (ገላ 5፡16)። ከእንግዲህ በእምነት እንጂ በሚያየው፥ በሚሰማው ወይም በስሜቱ በመመራት አይመላለስም፤ ምክንያቱም «ዓለምን የሚያሸንፈው እምነታችን ነው» (1ኛ ዮሐ. 5፡4)። በዋስትናና በተስፋ እየኖረ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቶሎ እንደሚመለስ በመጠባበቅ ይጠናከራል። ለዘላለም የሚኖረውን የእግዚአብሔር ፍቅር በመለማመድ ይኖራል።

«ልበ-ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና» (ማቴ. 5፡8)። ንጉሥ ዳዊት ከዚያ ሁሉ ሀብቱና በጠላቶቹ ላይ ከተቀዳጃቸው አያሌ ድሎች ባሻገር፥ በገዛ ልቡ ውስጥ ከሁሉም የላቀ ጦርነት እየተካሄደ እንዳለ በማወቁና ጥልቅ መንፈሳዊ ጉድለት እንደ ሰፈነበት በመገንዘቡ፡- «አቤቱ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፥ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ» በማለት ጸልዮአል [መዝ. (51)፡ 10]። እንደዚሁ ሁሉ፥ ማንም ሰው እንደ ዳዊት በእውነተኛ ንስሐ ወደ እግዚአብሔር ቀርቦ ንጹሕ ልብ እንዲፈጥርለት ካልጠየቀ በቀር፥ ልቡን ሊያነጻ ወይም ንጹሕ ልብ ሊፈጥር አይችልም። እግዚአብሔር በሕይወትህ አዲስ ነገር ለማድረግ ይፈልጋል። የገዛ መልካምነትህን ለማደስ የተቀዳደደ አዳፋ ልብሶችን መጠገኑ ልብህን ለእግዚአብሔር መኖሪያ የሚገባ ምቹ ስፍራ አያደርገውም። እርሱ ግን ቀጣዩን የተስፋ ቃል ስለሰጠህ፥ አንተን ለመርዳት እጅግ ፈቃደኛ ነው፡- «እናንተም ትጠራላችሁ፥ ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ። አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም አስሄዳችኋለሁ፥ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ»

Copyright ANCP

(ሕዝ. 36፡25-27)። ይህ እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሰጠን የአዲስ ኪዳን መልእክት ነው።


በዚህ ሥዕል በተጨማሪ የምንመለከተው የመልአኩን ለዳግመኛ ጊዜ መምጣት ነው። መላእክት ጌታን የሚያከብሩትን እንዲጠብቁና ከአደጋም እንዲያድኑአቸው የሚሾሙ ናቸው [መዝ. (34)፡7፤ (91)፡11፤ ዳን. 6፡22፤ ማቴ. 2፡13፤ 13፡39፤ 18፡10፤ የሐዋ. 5፡19፤ 12፡7-10)።

ሰይጣንም እንደዚሁ በሥዕሉ ላይ እንደሚታየው ወደ ቀድሞ ቤቱ ዳግም ለመግባት አጋጣሚ እንደሚጠብቅ ሆኖ፥ ከልብ አቅራቢያ ቆሞአል። ለዚህም ነው «በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጐ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና» የሚል ማስጠንቀቂያ የተሰጠን (1ኛ ጴጥ. 5፡8)። ብዙውን ጊዜ ግዴለሽ የሆኑትን እየፈተነ የብርሃንን መልአክ መስሎ ይቀርባል፤ የተመረጡትን እንኳ በብልሃት ለማታለል ይጣጣራል። ይህም ሆኖ፥ ከተቃወምነው ዲያብሎስ ከኛ ይሸሻል (ያዕ. 4፡7)።

## ስድስተኛው ሥዕል

ይህም የኮብላይን ሕይወት የሚያሳይ አሳዛኝ ሥዕል ነው። አንደኛው ዓይን መጥፋት ጀምሮአል፤ ይህም የልቡን እየቀዘቀዘ መሄድና በክርስትና ሕይወቱ እንቅልፍ እያበዛ መምጣቱን ሲያመለክት፥ ሌላኛው ዓይን ደግሞ ከዓለም ጋር ፍቅር ለመመሥረት ኃፍረት በራቀው ሁኔታ ዙሪያ-ገባውን እያማተረ ነው።

Copyright ANGP




6. ለፈተና የተጋለጠና የተከፋፈለ ልብ

በልቡ ውስጥ ያለው ብርሃን እየደበዘዘ ሲሄድ፥ ከክርስቶስ ጋር ለመሠቃየት የነበረውን ዝግጁነት የሚያሳዩት ሥዕሎች ቀጥ ብለው ለመቆም ባለመቻላቸው ወድቀዋል። ፈተናዎቹን መቋቋም አቅቶት ቀስ በቀስ እጅ በመስጠቱ ዙሪያውን ከበውታል። የእግዚአብሔርን ድምፅ በመስማት ፈንታ፥ የዲያብሎስን የብልጠት አሳቦችና የውሸት የተስፋ ቃሎች ማዳመጥ ጀምሯል። ምንም እንኳን ሃይማኖተኛ ቢመስልና ለዓለም ነገሮች ያለውን ፍላጎት ከውስጡ እየደበቀ ወደ ቤተ ክርስቲያን መመላለሱን ቢቀጥልም ቅሉ፥ በልቡ ውስጥ ለእግዚአብሔር የነበረው ፍቅር ቀዝቅዞአል። በመንታ መንገድ ላይ ቆሞ ያመነታል። ከዓለም ነገሮች ጋር እየተጫወተ፥ እግዚአብሔርን እንደሚወድ ለማሳየት ይሞክራል። ሕሊናውን በልቡ ውስጥ የሚወክለው ኮከብ እየደበዘዘ በመሄድ ላይ ነው። መስቀሉን የሚሸከመው በፈገግታ ስላልሆነ እንደ ከባድ ሸክም አድርጎ ይቆጥረዋል። እምነቱ መናጋት ስለሚጀምር፥ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት መገናኘቱን ያቆምና በልቡ ውስጥ ለሚገኙ ሁኔታዎች ግድየለሽ በመሆን፥ ከልቡ ውጭ ለሚጠባበቀው ዲያብሎስ ስፍራ ያዘጋጃል። ከእውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች ይልቅ የኃጢአተኞችን ኅብረት ይናፍቃል።

ትዕቢትን የሚወክለው ብርቅዬው ወፍ ተመልሶ የሚገባበትን በር ማየት ይጀምራል። በጸጋ ብቻ መዳኑን በመዘንጋት ኩራተኛ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል። የሚያሰክር መጠጥ ፍላጎት የልቡን በር ያንኳኳል። ሰይጣን ይህ አንድ አጋጣሚ መንፈሳዊ ሕይወቱን እንደማይጎዳ አድርጎ የሚነግረው ከኃጢአተኛ ጓደኞቹ መካከል ተለይቶ መገኘት በሚያሳፍረው በአንድ ልዩ ወቅት ሊሆን ይችላል። በዚህም ጊዜ መንፈሳዊነት የጎደላቸው አሳቦችና መሻቶች መታየት ይጀምራሉ። ምናልባትም አሳፋሪ ቀልዶችን ማዘውተር፥ አግባብነት የጎደላቸውን ሥዕሎች ደጋግሞ ማየት፥ በአልባሌ ጓደኝነት መጠመድ፥ ወደ ዳንስ ቤቶች (የጭፈራ ቦታዎች) መሄድ፥ ከፉ ዓለማዊ መዝናኛዎችን መከታተል፥ የሰብዓዊ ተፈጥሮ ክሥተት

Copyright ANGP

ለንጂ ስሕተት እንደሌለበት የሚናገረውን የዲያብሎስን ኃጢአታዊ ምክሮች ወደ ልቡ የማስገባት ዝንባሌ ሊታይበት ይችላል።

እንደ እውነቱ ከሆነ፥ የክፋት መልእክተኞች የሆኑ የዱር ወፎችና ጠማማ አሳቦች ከጭንቃላታችን በላይ ቢበሩ ምንም ልናደርጋቸው አንችልም፤ ይሁንና ሕይወታችንን በመቆጣጠርና ክፉ ተግባሮቻቸውን በማራባት በልባችን ውስጥ ጐጆአቸውን እንዲሠሩ ብንፈቅድላቸው ጥፋተኞች ነን። ለዲያብሎስ ትንሿን ጣታችንን ብንሰጠው፥ ጠቅላላውን እጃችንን በመውረር ነፍስና መንፈሳችንን ወደ ዘላለማዊ ገሃነም እንደሚስበው የተረጋገጠ ነው። ስለሆነም፥ የወጣትነትን ምኞቶች በማስወገድ፥ በማንኛውም መንገድ ቢመጣም ከኃጢአት ጋር እንዳንጫወት እግዚአብሔር በብርቱ ያስጠንቅቀናል። ጠባቂና ተከላካይ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ ሩጥ።

በዚህ ሥዕል ልብን በቢላዋ የሚወጋው ሰው በክርስትና ላይ የሚሳለቁትንና የሚቃወሙትን ያመለክታል። በሐሰተኛ ምላሳቸውና በሚያላግጥ አፋቸው የክርስቲያኖችን ልብ ያቆስላሉ፤ ይህም የተከፋፈለ ልብ የማይቃወመው ጥቃት ነው። ከእግዚአብሔር በላይ ሰዎችን በመፍራትና ሰዎች ስለሚሉትና ስለሚያደርጉት በመስጋት፥ የሰዎች ባሪያ ይሆንና ከእግዚአብሔር ፊቱን ያዞራል። የመከራና የኃዘን ጊዜ ሲደርስ ቁጣና ንዴት ብቅ ይሉና ወደ ውስጥ ለመግባት ይታገላሉ። ሌሎች ሰዎች የበለጠ ስኬታማና ባለጠጋ በሚሆኑበት ጊዜ የሚመጣው ክፉው የቅንዓት እባብ ትንሽ በር ከተከፈተለት ያለማስጠንቀቂያ ዘልቆ በመግባት ለጥላቻና ለትዕቢት በሩን ወለል አድርጎ ይከፍታል።

«ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ» (ማቴ. 26፡41) የሚለውን የጌታችንን ማስጠንቀቂያ ካልተከተልን በቀር የገንዘብ ፍቅር ወደ ልባችን በቀላሉ ሊገባ ይችላል። «ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» (1ኛ ቆሮ. 10፡12)።

Copyright ANGP

የዲያብሎስን ክፉ ማታለል ተቋቁመን እንድንቆም እግዚአብሔር የሚሰጠንን ትጥቆች ሁሉ መልበስ አለብን (ኤፌ. 6፡ 11-18)።

## ሰባተኛው ሥዕል

ይህ ሥዕል በአንድ ወቅት የእግዚአብሔር ብርሃን ከበራለት፥ የሰማይን ስጦታ ከተቀበለና የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ከተለማመደ በኋላ እምነቱን በመተው የኮበለለውን የሰው ልብ ሁኔታ ያሳያል (ዕብ. 6፡4)። «መልካም የምሥራች» ተብሎ የተጠራው የወንጌሉ እውነት ከቀረበለትና ከተገለጸለት በኋላ ፍጹም ንስሐ ያልገባውን ወይም ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ያልሰጠውን ሰው ሁኔታ ያመለክታል። እግዚአብሔር በሚናገረው ጊዜ ልበ-ደንዳና የሆነ ሰው ሕይወቱን ለመለወጥ ከሚያደርጋቸው እርባና-ቢስ ጥረቶች ባሻገር ይብስ እየከፋ ይሄዳል።


ኢየሱስም ራሱ፡- «ርኩስ መንፈስ ከሰው በወጣ ጊዜ ዕረፍት እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል፤ ባያገኝም፡- ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤ ሲመጣም ተጠርጎ አጊጦም ያገኘዋል። ከዚያ ወዲያ ይሄድና ከእርሱ የከፉትን ሌሎችን ሰባት አጋንንት ከእርሱ ጋር ይይዛል፥ ገብተውም በዚያ ይኖራሉ፤ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ይብስበታል» በማለት ገልጾታል (ሉቃስ 11፡24-26)። «ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል ደግሞ፡- የታጠበች እርያ በጭቃ ለመንከባለል ትመለሳለች እንደሚባል እውነተኞች ምሳሌዎች ሆኖባቸዋል» (2ኛ ጴጥ. 2፡22)።

እነዚህ ጥቅሶች የኮብላይን ወይም ንስሐ የማይገባን ኃጢአተኛ የልብ ሁኔታ በትክክል ይገልጻሉ። ኃጢአት በአታላይነቱ ሁሉ ዳግም ልብን ለመቆጣጠር መጥቷል። ፊቱም ሳይቀር በተወሰነ ደረጃ የልቡን ሁኔታ ይገልጻል። ኃጢአትና መንፈስ ቅዱስ አብረው ሊኖሩ ስለማይችሉ በየዋህ ርግብ የተመሰለው መንፈስ ቅዱስ ከልብ ለመውጣት ይገደዳል። ልብ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና የሰይጣን መሸሸጊያ ሊሆን አይችልም። የእግዚአብሔርን ቃል የሚያመለክተው መልአክ እንደ ጠፋው ልጅ ንስሐ ይገባ (ትገባ)

Copyright ANGP

ይሆናል ብሎ ተስፋ እያደረገና ወደኋላ ዞሮ እየተመለከተ በኀዘን ከልብ ዙሪያ ይርቃል «እርያዎችም ከሚበሉት አሰር ሊጠግብ ይመኝ ነበር፥ የሚሰጠውም አልነበረም። ... ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና፡- አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም» (ሉቃስ 15፡16-20)። አባትም በኀዘን የተቆራመተውን ልጁን ይቅር ብሎ በደስታ ተቀበለው።

Copyright ANGP




7. ኮብላዩ ወይም ደንዳናው ልብ

በዚህ ሥዕል ውስጥ የሚታየው ልብ የእውነተኛ ንስሐ ምልክት የለውም፤ ወደ እግዚአብሔር መመለስም ሆነ በኢየሱስ እግር ሥር ወድቆ ይቅርታን መፈለግ አይስተዋልበትም። በመሆኑም ልክ ሕሊናው በጋለ ብረት ተቃጥሎ ለዝምታ የተዳረገ ይመስላል። ጆሮዎች ቢኖሩትም የኢየሱስን ተለማማጭ ድምፅ አይሰማም። ዐይኖች ቢኖሩትም ከእግሩ ሥር ተከፍቶ የሚገኘውን ትልቅ የሲኦል ጉድጓድ አይመለከትም። ዐይኖች በኃጢአቱ መቀጠል አሳፋሪ ነገር መስሎ አይሰማውም። ሰይጣን በልብ ውስጥ ሊነግሥ፥ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦአል። «በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጥ ግን የሙታን አጥንት፥ ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ፥ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን» ይመስል ሃይማኖታዊ መልክ በመያዝ ውጫዊ ጭምትነትና አክብሮት ሊኖረው ይችላል(ማቴ. 23፡27)።

የውሸት አባት የእውነትን መንፈስ ስፍራ ይይዛል። ማንኛውም እንስሳ፥ማንኛውም ኃጢአት ከልዩው አጋንንት ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ በመመላለስ ልቡን ይመረዋል። ምንም እንኳ ከነዚህ አሠቃቂ ነገሮች ነፃ ለመሆን ቢፈልግም አስረው ያቆዩታል። «የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፤ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ፥ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?» (ዕብ. 10፡28-29፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡1-14)።

ውድ ወዳጄ፥ ይህ ሥልጣን ያንተን ልብ የሚመስል ከሆነ አሁኑኑ ከልብህ ወደ እግዚአብሔር እንድትጣራ እመክርሃለሁ። «እርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል» (ዕብ. 7፡25)። እንዲሁም፥ በእውነተኛ ንስሐ አቅርበህ፥ ኃጢአትህን ሁሉ ይቅር ለማለት ሙሉ ፈቃድና ብቃትም አለው። በልብህ ውስጥ እንዲሠራ ፍቀድለት እንጂ፥ዲያብሎስንና አጋንንቱን ሁሉ ሊከለክልና ከልብህም ጭራሽ ሊያስወግድ ይችላል። «ለምጻሙ ወደ እርሱ መጥቶ

Copyright ANCP

ተንበረከከና ፡-«ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ» ብሎ ለመነው።ኢየሱስም አዘነለት እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና ፡- እወድዳለሁ ንጻ አለው » (ማር. 1፡40፣ 41)። ይሁንና፥በልብ ደንዳናነትህ ብትቀጥልና ከበርሃን ይልቅ ጨለማን ብትመርጥ፥ ተስፋም ሆነ እገዛ አይኖርህም ከሕይወት ይልቅ ሞትን መርጠሃልና። ኃጢአትም ዋጋውን ይከፍልሃል እርሱም ሞት ነው !(ሮሜ. 6፡23።

## ስምንተኛው ሥዕል

በዚህ ሥዕል ላይ፥ ክርስቶስን ለመከተል የሚወስንባቸውን ጊዜያት በከንቱ በማሳለፍ፥ ወደ ሞት የሚቃረበውን የልበ-ደንዳናውን ኃጢአተኛ ልብ እንመለከታለን። የዚህም ሰው ሰውነት በሥቃይ የተሞላ፥ ነፍሱም በሞት ፍርሃት የተሸበበች ሊሆን ይችላል። ሞት (ዐፅም) ባልተጠበቀና ባልተፈለገ ሰዓት መጥቷል። ውሸትንና የኃጢአት ምኞቶች ገሸሽ ብለው የሄዱ ሲሆን፥ ከፍተኛና አስጨናቂ የሆነው የኃጢአት ዋጋ አስፈሪ እውነታ ቀርቧል። የገሃነም ሥቃዮች እውን ሆነውበታል። ምንም እንኳ ለመጸለይ ቢናፍቅም፥ ለረዥም ጊዜ ፍቅሩን ለመቀበል ችላ ይለው ከነበረው ከእግዚአብሔር ጋር ሊገናኝ እንደማይችል ይሰማዋል።

Copyright ANCP




8. የኃጢአተኛው ፍርድ

ወዳጆቹ ከአልጋው ጥግ ለመድረስ የፈሩ ሲሆን፥ ባዶ የማጽናኛ ቃሎቻቸውም ሊረዱት አይችሉም። ብልጽግና ሕይወቱን ሊያስረዝም፥ ነፍሱን ሊያድን ወይም የነፍሱን ሥቃይ ሊቀንስ አይችልም። ዲያብሎስ ምንም የማመዛዘን ዕድል ስለማይሰጠው፥ በእግዚአብሔር ላይ መደገፉ የማይሆን ይመስለዋል።

በአንድ ወቅት ይወደውና ይኖርለት የነበረው ማናቸውም ነገር ሁሉ አሁን መሳቂያና መሳለቂያ ያደረጉት ይመስለዋል፤ የእግዚአብሔርን ፍቅር ስለጣለና ከፍርዱም በታች ስለወደቀ፥ የትኛውም የማይታመንና ምናልባትም ያልዳነ የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋይ፥ ቄስ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪ ሊረዳው አይችልም። በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ አስፈሪ ነገር መሆኑን መረዳት ይጀምራል (ዕብ. 10፡31)። ተስማሚ ጊዜ ሲያገኝ ወይም ወደ ሞት በሚቃረብበት ጊዜ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ተስፋ ሲያደርግ ነበር፤ አሁን ግን ጊዜው እንዳለፈ ይመለከታል። በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱበትን ዕድል ሳያገኙ ጋደም ባሉበት አልጋ ላይ ሞተው ይገኛሉ። በመሆኑም፥ እግዚአብሔር ቀርቦ ሳለ ወደርሱ መመለሱ አስፈላጊ ነው። ለመሞት በማጣጣር ላይ ያለው ኃጢአተኛ በሕይወት ዘመኑ የእግዚአብሔርን ይቅርታና ፍቅር ስላልተቀበለ፥ የእግዚአብሔርን አጽናኝና አዳኝ ቃላት በመስማት ምትክ አሁን በዳኝነቱ የሚሰጠውን ፍሬ ይሰማል፤ ዳኛውም እርሱ ሊቀበለው ያልፈለገው አዳኝ ሲሆን፥ «እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ» በማለት ይፈርድበታል (ማቴ. 25፡41)። «ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ» ተመድቦባቸዋል (ዕብ. 9፡27)።

## ዘጠንኛው ሥዕል


ይህ ሥዕል በታማኝነቱ ጸንቶ፥ በሚያሠቃዩ ፈተናዎች ላይ ድል የሚቀዳጀውን ክርስቲያን ያሳያል። በነገር ሁሉ ቢፈተንም፥ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ድል በመንሣት፥ እስከ መጨረሻው

Copyright ANCP

ጸንቶ ይቆማል። በክርስትና ውድድር ውስጥ መካፈል ብቻ ሳይሆን፥ «የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን» እንድንጓዝ በሚያሳስብ አሳብ ላይ ተመሥርቶ (ዕብ. 12፡1-2)፥ ሩጫውን ይቀጥላል።

ሰይጣን ከአጋንንቶቹ ሁሉ ጋር በእግዚአብሔር በመሆን የሚያምንበትን ሰው ልብ ይከባል፤ ይህንንም የሚያደርገው የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ሰው ወደ ጥፋት ለመምራት ቢሆንም፥ ዳሩ ግን ከቶውንም አይሳካለትም። በሥዕሉ ላይ ትዕቢት፥ የገንዘብ ፍቅር፥ ምግባረ-ብልሹነት እና ሌሎችም ተመልክተዋል። በነብሩ ምትክ አህያ መቅረቡም፥ ብዙውን ጊዜ ኃጢአት ወደ እኛ ጎራ የሚለው በሌላ መንገድ ወይም በሌላ ቅርጽ ወይም በሌላ ስም ከለላ ሥር በመሆኑ ነው። ይህም ሆኖ፥ ንቁውን ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ስለሚመሩት፥ በሃይማኖት ስም ወይም የብርሃን መልአክ በመምሰል ቢመጣም እንኳ ኃጢአት መሆኑን ያውቃል። በአንድ እጁ የመጠጥ ዋንጫ የጨበጠው ሰው፥ በክርስቲያኑ ዙሪያ እየደነሰና እየጨፈረ፥ ሐሰተኛ በሆነ ዓለማዊ ደስታ ሊፈታተነው ይሞክራል። ይሁንና፥ ኃጢአትንና ዓለማዊ ምኞቶችን በተመለከተ ከክርስቶስ ጋር ስለሞተ፥ ይህ ራሱን ለጌታ አሳልፎ በሰጠው ክርስቲያን ላይ የሚያስከትለው ለውጥ አይኖርም። በሥዕሉ ውስጥ የሚገኘው ሌላው ሰው ክርስቲያኑን በጨቤ ይወጋዋል። ከማያምኑና ብዙውን ጊዜ አምነናል ከሚሉ ሰዎች የሚሰነዘሩ ስድቦች፥ ሐሜቶች፥ ፌዝና ዛቻዎች፤ የእውነተኛውን አማኝ ልብ ለማቁሰል ይሞክራሉ። ዳሩ ግን ይህን መሰሉ ክርስቲያን ሰዎች ስለሚሉት ነገር ግዴለሽ ሆኖ፥ እግዚአብሔር የሚለውን ብቻ ለማድረግ ይተጋል። «ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ» (ማቴ. 5፡11-12) የሚሉትን የኢየሱስን ቃላት ያስታውስና በዚሁ ይጽናናል።

Copyright ANCP




9. ድል-ነሺ ልብ

ኃጢአተኛው ተፈጥሮአችንና ዲያብሎስ በመተባበር ክርስቲያኑን ከእግዚአብሔር ፍቅር ለመለየት ባለማቋረጥ ይጣጣራሉ። ይሁንና፥ ቆራጡ ክርስቲያን በታላቅ ደስታና ድፍረት፡- «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን ... በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን!» ሊል ይችላል (ሮሜ 8፡35፥ 37)። የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃዎች ሁሉ በመልበስ፥ ክፉ ቀን በሚመጣበት ጊዜና እስከ መጨረሻው ከተዋጋ በኋላ፥ የዲያብሎስን ጥቃቶች ሊቋቋም ይችላል። እኛ በርሱ አማካኝነት ድልን እንድንቀዳጅና ለመቼውም ቢሆን ድምቀቱ የማይደበዝዘበትን የከበረ አክሊል እንድናገኝ፥ ክርስቶስ በሁሉም ፈተናዎች ላይ ድልን የተጐናጸፈ ነው (ኤፌ. 6፡10-18፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡4)።

የዚህ ዓይነቱ ክርስቲያን የሕሊናው ኮከብ ንጹሕና ደማቅ ነው። ልቡም በእምነትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ነው። መልእኩ እንደ እግዚአብሔር ቃል፥ ድል ለሚነሡና እስከ መጨረሻው ለሚጸኑት ስለሚሰጡ የበለጸጉ በረከቶች ያስታውሰዋል። «ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ።» «ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጐዳም።» «ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፤ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል።» «ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻው ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ።» «ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጐናጸፋል፥ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፥ በአባቴና በመላእክቱም ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ።» «ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፥ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም።» «እኔ ደግሞ ድል እንደነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ

Copyright AHGP

ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ» (ራእይ 2፡7፥ 11፥ 17፥ 26፤ 3፡5፥ 12፥ 21)።

ልቡ ብቻ ሳይሆን ገንዘቡም ጭምር ለእግዚአብሔር ስለ መስጠቱ የተከፈተው የገንዘብ ከረጢት ያሳያል። ገንዘቡን ከማባከን ይልቅ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር በማዋል ድሆችን ይረዳል፤ አሥራት (የገቢውን አንድ አሥረኛ) ያዋጣል። ለድሆች ከመመጽወትም አልፎ ያለውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሰጣል።

ዳቦውና ዓሣው በንጽሕና ራሱን ገዝቶ እንደሚኖር ያሳያል። ጠንካራ መጠጥ በመጠጣት ወይም ርኩስ ምግብ በመብላት፥ ሕይወቱን አያበላሽም (የሐዋ. 15፡20)። ገንዘቡን በማባከንም ሆነ፥ በማንኛውም መልኩ ትምባሆ በመውሰድና ጫት በመቃም (የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆነውን) ሰውነቱን ከማበላሸት የታቀበ ነው፤ ሱስ በሚያስይዙ ዕፆችም ሆነ ጎጂ መድኃኒቶች አይጠቀምም። ይልቁንም ንጹሕና ተገቢ አልሚ ምግቦችን ይመገባል። የራሱ ልብ የጸሎት ቤት ሆኗል። በተጨማሪም በሁሉም የአየር ጸባዮችና ሁኔታዎች፥ የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ፕሮግራሞችን አዘውትሮና አክብሮ ይከታተላል። ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት እስካልተገናኘ ድረስ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንደማያድግ ስለሚያውቅ፥ በቤተ ክርስቲያን ወይም ከቤተሰቡ ጋር በራሱ ክፍል ... መጸለይን ይወዳል።

የተከፈተው መጽሐፍ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ለርሱ ምንጊዜም እንደተ ከፈተ መሆኑን ያሳያል፤ በመሆኑም፥ በየቀኑ እያነበበው፥ ጥበብንና ብርታትን፥ ሕይወትንና ብርሃንን፥ እንዲሁም ዕልቆ-መሳፍርት የሌላቸውን ብልጽግናዎች ያገኝበታል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚመራበት መብራት፥ ብሎም ዲያብሎስን የሚያሸንፍበት ሰይፍ በመሆን ይረዳዋል። ቃሉ የነፍሱ የየዕለቱ መንፈሳዊ ቀለብ፥ የጥማቱ ማርኪያ ውኃ፥ የእድፍ ማስወገጃ መታጠቢያ ገንዳ፥ ራሱን የሚያይበት መስተዋት ነው።

Copyright ANGP

ያለመስቀል ሽልማት እንደሌለ ስለሚያውቅ መስቀሉን በደስታ ይሸከማል። ከክርስቶስ ጋር ከሞት በመንሣት አዲስ ሕይወት መኖር እንዳለበት ሲያስብ በሰማያዊ ነገሮች ላይ ልቡን ይጥላል፤ በምድራዊ ሳይሆን በዚያ በሚገኙ ነገሮች ላይ አእምሮውን ያሳርፋል (ቈላ. 3፡1-2)። በተገቢው ሰዓት ፍሬ እንደምትሰጥ፥ በውኃ ምንጭ ዳር እንደተተከለች ዛፍ፥ በርካታ ፍሬ እንደምታፈራ እውነተኛ የወይን ግንድ፥ በመንፈስ ፍሬ ተሞልቶ እግዚአብሔርን ለመገናኘት ይዘጋጃል (መዝ. 1፡3)። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተቀበለው ፍጹም የእግዚአብሔር ፍቅር ልቡን ስለሞላው የሞት ፍርሃት አያውከውም።

## አሥረኛው ሥዕል

ኢየሱስ፡- «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም» (ዮሐ. 11፡25-26)። «ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም» (ዮሐ. 5፡24)። ሞት በክርስቲያን ላይ የሚያሳድረው ፍርሃት ወይም ቅጣት የለም። «ሞት ድል በመንሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል። ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ? ... በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን» (1ኛ ቆሮ. 15፡54-57)።

ከእግዚአብሔር ጋር የኖረና የተመላለሰ ሰው ሞትን አይፈራም። የሚሞትበትም ጊዜ ሲደርስ፥ ሐዋሪያው ጳውሎስ፡- «ልሄድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፥ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና» እንዳለው (ፊልጵ. 1፡23)፥ በደስታ ወደ ማደሪያው ይጓዛል።

ክርስቲያን ለርሱ በመሞት፥ በመስቀል ላይ ለኃጢአቱ ዋጋ የከፈለለትን የኢየሱስን ፊት ለማየት ይናፍቃል። እንዲሁም መንፈስ

Copyright AHCP

ቅዱስ የኢየሱስን ቃላት ያስታውሰዋል፡- «ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ ... ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ» (ዮሐ. 14፡1-4)። «ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው» (1ኛ ቆሮ. 2፡9)። በዚህ ምድር ላይ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ፈለግ ተከትለው ለተመላለሱ ቅዱሳን የተዘጋጀችውን የሰማያዊት ከተማ ክብር ለመግለጽ የሚችል ምድራዊ ቋንቋ አይገኝም።

Copyright ANGP




10. በክብር ወደ ቤት መሄድ

በዚህ የመጨረሻው ሥዕል ውስጥ በሚያስፈራራው ዐፅም (ሞት) ምትክ የእግዚአብሔር መልአክ ወይም መልእክተኛ ቀርቦአል። የሰውየው ነፍሱና መንፈሱ በሟች ሥጋ ውስጥ ከመታሰር ተለቀው ወደሚወደውና በመስቀል ላይ ወደሞተለት ኢየሱስ በክፍት የሰማይ በሮች ያርጋል። እግዚአብሔር ባለበት በዚያ ስፍራ ጌታውና አምላኩ «መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ ... ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» (ማቴ. 25፡21) የሚሉ የምስጋና ቃላትን በማቅረብ፥ ደስ የሚያሰኝ አቀባበል ያደርግለታል። ከእንግዲህ ሰይጣን በርሱ ላይ ምንም ቁጥጥር ሊያደርግ አይችልም፡- «ድሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት» (ሉቃስ 16፡22)። «ከሰማይ፡- ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው። መንፈስም፡- አዎን፥ ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ፥ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ» (ራእይ 14፡13)።

## የመጨረሻ ምክር

ውድ አንባቢ ሆይ፥ እግዚአብሔር አሁን በሙሉ ልብህ ወደ እኔ ተመለስ በማለት እየተናገረህ ስለሆነ፥ ለሚወድህ አምላክህ ልብህን እንድትሰጠው እግዚአብሔር ይርዳህ (ዘዳ. 30፡2)። የዛለውን፥ በትካዜ የተዋጠውንና የቆሰለውን ልብህን ለኢየሱስ ብትሰጠው እርሱ ደግሞ አዲስ ልብና አዲስ አእምሮ ያጐናጽፍሃል። ሰውን የምግባር ጉድለት የሞሉባቸውን ነገሮች እንዲያደርግ የሚገፋፉት ክፉ አሳቦች የሚመነጩት ከሰው ልብ ስለሆነ (ማር. 7፡21)፥ ለአታላዩ ልብህ አትሸነፍለት ወይም ለከንቱ ምኞቶቹ አትደለልለት። ኃጢአትህን ተወውና መልካም የሆነውን ምረጥ። ለምን? ምክንያቱም «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው» (ሮሜ 6፡23)።

Copyright ANGP

አንተም ሕይወትህን ለእግዚአብሔር የሰጠኸው ሰው፥ «በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ እምነትና ፍቅር አድርገህ፥ ከእኔ የሰማኸውን ጤናማ ቃል ምሳሌ ያዝ» (2ኛ ጢሞ. 1፡13)። ጳውሎስ አሁን በተመሳሳይ ለተመሳሳይ ምክንያት የተነሣ፥ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 1፡12 ላይ፥ «ያመንሁትን አውቃለሁና፥ የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ» ይላል። በእግዚአብሔር ላይ ባለህ እምነት ራስህን በማነጽ፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየጸለይህ ራስህን በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ጠብቅ፤ በዚህም ሁሉ መንገድ፥ እውነትና ሕይወት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ዓይኖችህን አኑር፤ እርሱም ፈጥኖ በመመለስ ልጆቹን ይወስዳቸዋል- «የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ» (1ኛ ጢሞ. 6፡15)።

«ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ፥ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆማችሁ ለሚችለው ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን ከዘመን ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘላለምም ድረስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁን፤ አሜን» (ይሁዳ ቁጥር 24 እና 25)።

Copyright ANCP

**A SPECIAL WORD FROM ANGP**
**UN MONDE SPÉCIAL DE L'ANGP**
**UMA PALAVRA ESPECIAL DA ANGP**

**This booklet "The Heart of Man" is available in over 538 languages and dialects spoken throughout the world (Africa, Asia, The Far East, South America, Europe, etc.) Our Heart Book is now also available on cell phones, tablets, etc from www.angp-hb.co.za or as an APP "Heart of Man" on Android phones.**

**Le livre du "Coeur de l'homme" peut etre obtenu en plus de 538 langues et dialectes parles dans le monde entier, a savoir: Afrique, Amerique, Asie, Extreme Orient, Europe. Notre Livre du Coeur est maintenant aussi disponible sur votre Telephone cellular, plaques, etc. de www.angp-hb.co.za ou comme une Application "Heart of Man" sur telephones Android.**

**Este livro "O Coracao do Homem" e obtfdo em mais de 538 linguas e dialectos falados em todo o mundo, a saber: (Africa, Asia, America do Sul, Extremo Oriente, Europa, etc). O nosso Livro O Coração do Homem tambem esta agora disponivel em telefone celular, tablets, etc. de www.angp-hb.co.za ou como um aplicativo "Heart of Man" nos telephones celulares Android.**

Copyright ANGP

**The 10 heart pictures contained in this booklet are also available in the form of large coloured picture charts (86 x 61cm) bound together in a set of 10 pictures. These "Heart Charts" can be obtained with European or African features and are particularly suitable to be used in conjunction with the Heart Book for class-teaching, open air evangelization etc. Kindly contact us to ascertain the latest subsidized price of this chart.**

**Les 10 images du coeur qui figurent dans ce livre peuvent etre obtenues en tableaux de couleur, format 86 x 61 cm, avec des physionomies europeennes ou africaines. Ils peuvent etre utilises en meme temps que le livre du coeur pour des classes bibliques, a**

l'ecole du dimanche ou lors de reunions de plein air. Soyez aimable de nous contacter pour assurer les derniers prix en cours du tableau.

As 10 imagens do coracao, contidas neste livro podem ser obtidas num conjunto de 10 imagens em colorido no tamanho de (86 x 61 cm). Estes "Cartazes do Coracao podem ser obtfdos com caracterfsticas Europeias e Africanas e podem ser usados em conjuncao com o mesmo livro em classes de ensino biblico, evangelizacao ou ao ar livre. Agradeciamos que nos contacta- se para confirmacao do ultimo preco dos cartazes.



Kindly write to us if you are able to assist us with further translations of our free Gospel literature, informing us of the language into which you could translate this Gospel literature. Your assistance would be appreciated.

Copyright ANGP

If you have found salvation in Christ, or have been otherwise blessed through our Gospel literature, please let us know. We would like to thank God with you, and remember you further in our prayers.

Nous vous invitons a nous contacter pour faire des arrangements concernant de nouvelles traductions de notre litterature, nous informant de la langue dans laquelle vous pouvez traduire cette litterature evangelique. Votre aide sera beaucoup appreciee.

Si vous avez trouve le salut en Christ ou si vous avez ete beni par notre litterature, nous vous prions de nous le faire savoir. Nous aimerions remercier Dieu avec vous et prier pour vous.

Nos vos convidamos a nos contactar, afim de fazer qualquer arranjo concernente a novas traducoes de nossa literatura em outras lfnguas. Vossa assistencia sera muito apreciavel.

Se tem encontrado a salvacao em Cristo, ou se tem sido abencoado por intermedio da nossa literatura evangelica, faca o favor de nos

informar. Pois nos gostarfamos de agradecer a Deus juntamente convosco, e lembra-lo sempre em nossas oracoes.

For free Gospel literature, books and tracts in over 538 languages, write to:

Pour obtenir gratuitement de la litterature evangelique, des livres et des traites en plus de 538 langues, ecrivez a:

Para obter gratuftamente a literatura evangelica, livros e folhetos em mais de 538 lfnguas diferentes escreva para:


E-MAIL: info@angp-hb.co.za
info@angp.co.za

**ALL NATIONS GOSPEL PUBLISHERS**

**P.O. Box 2191**

**PRETORIA**

**0001**

**R.S.A.**


Copyright ANGP

A Gospel Literature Mission financed by donations

Une Mission de litterature evangelique financee de dons

Missao de literatura Evanqelica financiada por donativos

(Reg. No. 1961/001798/08)